# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)

ጥቅምት ፱ ቀን 2009 ዓ. ም

## የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከውድቀት አያድንም!

አንድ መንግሥት በአገሩ ላይ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ በሚያጋጥመው ጊዜ የአገሪቱን ሀብትና የሰውን ጉልበት አቀነባብሮ የደረሰውን አደጋ ለመታደግ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ አንድ ወራሪ መንግሥት የሌላን ሀገር ድንበር በኃይል ጥሶ ከገባ ድንበር የጣሰውን ጠላት ለመቋቋም የሚያስችል ኃይል ለመገንባት እንዲቻል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ይታወጃል።

በዚህ መሠረት በዓለም ዙሪያ በርካታ መንግሥታት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን በሕገ-መንግሥታቸው ውስጥ አስፍረው መቼ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መጠራት እንዳለበትና በማንና ለምን እንደሚጠራ በግልጽ አስቀምጠዋል። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በአግባቡ ሥራ ላይ ከዋለ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ አንቀጽ ነው። በአንጻሩ ግን፣ በርካታ አምባገነኖች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ያለአግባብ በመጠቀም የዜጎቻቸውን መብት በመርገጥና ሥልጣናቸውን በጊዚያዊነትም ቢሆን ለማስቀጠል እንደ ዘዴ ሲጠቀሙበት ይታያል።

የህወሓት አገዛዝ እንዲሁ ከተወጠረበት ሁኔታ ለመውጫ ይጠቅመኛል ብሎ ስላሰበ፣ አንቀጽ 93ትን ተጠቅሞ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጇል። በትክክል የአዋጁ ዓቢይ ዓላማ ግን የመንግሥትን ኢ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ በመቃወም የተቀጣጠለውን የሕዝብ አመጽ ለማጨናገፍ፣ ለማኮላሸትና ከተቻለውም ጨርሶ ለማዳፈን ነው። በዚህ ድርጊቱም ህወሓት ከዚህ በፊት ከገደለው የበለጠ ብዙ ሕዝብ ሊጨርስ እንደሚችል መገመት አያዳግትም፣ ዋና ዓላማው ሕዝብን ረግጦ፣ አፍኖና ጨፍጭፎ በሥልጣን ላይ መቆየት ነውና። ዓላማው ይህ መሆኑ በግልጽ እየታወቀ፣ የመገናኛ ሚኒስተር ተብዬው ግን ሲያድበሰብስ አዋጁ የታወጀው በሕዝቡ አመጽና ሰልፍ ምክንያት አይደለም ይለናል። ይህን "ተጨፈኑ ላሞኛችሁ" አባባሉን አንድ ጣቱን የሚጠባ ልጅንም እንኳን ሊያታልል አይችልም። የአዋጁ መንፈስ

**P.O.Box 91384**
**Los Angeles, CA 90009**
**Phone: 202- 241 2078**
**Email Address**: **eprp-united@eprp-ihapa.com**

ፍጹም ግልጽና የማያሻም መሆኑ አሌ አይባልምና። የህወሓት ዋና ዓላማ በመግደል፣ በመደብደብና በፈለገ ጊዜም በየቤቱ እየገባ እያሰረ በመውሰድ አይበገሬ ተፋላሚዎችን በመጨፍጨፍ ትግሉን ማጨናገፍ ስለሆነ፣ በዚህ እኩይ ተግባሩ በዓለምአቀፍ የሰው ልጅ መብት ጥሰት እንዳይከሰስ ለሽፋን የዘረጋው መጋረጃ ነው። ይሁን እንጂ አመጹ እንደ እሳት እየተንቦገቦገ በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝቡ ቀዳዳ ተጠቅሞ መንግሥት ተብዬው እያደረሰበት ያለውን አፈናና ግድያ ለመቋቋም በመሆኑ፣ ህወሓት እስካሁን እየገደለና እያሰረ ካለው እርምጃ የተለየ ነገር ከአዋጁ ጀርባ ሆኖ አደርጋለሁ ብሎ ማለባበሱ የሕዝቡን ቁጣ ያባብሰዋል እንደሆን እንጂ ከቶውንም የሚመኘውን ለውጥ ሊያመጣለት አይችልም። ከዚህ አዋጅ የምንረዳው ሌላው ቁም ነገር ደግሞ በቴሌቪዥን እየወጡ ጥቂት ነውጠኞች እያሉ የሰፊውን ሕዝብ እይታ ሲያቃልሉት የነበረው የውሸት ፕሮፓጋንዳ መሆኑንና ይህ የአጣጣሉት የሕዝብ ትግል ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ያናወጣቸው መሆኑን ዓለም ሳይቀር መረዳቱን ነው።

ሕዝባዊ አመፅ ግብፅን ባናወጣት ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ብታውጅም፣ አኑዋር ሳዳትን ከሞት አላዳነውም፤ የፀደይ አብዮት የተሰኘውን የግብፃውያንን ሕዝባዊ ማዕበልም አላስቆመውም።

ህወሓት ከዚህ ሁኔታ ተምሮ ከአሁን በኋላ በሕዝባችን ላይ ከሚያደርገው ግድያ፣ ድብደባና እስራት ተቆጥቦ ሥልጣኑን ለሕዝብ በአስቸኳይ በሰላም እንዲያስረክብ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) በጥብቅ ይጠይቃል። ይህን የተፍረከረከ ሥልጣን ጠግኖ ለማቆየት በሕዝብ ላይ የሚደረገውን የኃይል እርምጃም በጥብቅ ያወግዛል።

ሕዝባዊ ትግሎ ተጋግሞ የህወሓትን አገዛዝ በሚያርበደብድበት ወቅት የተቃዋሚ ኃይሎች ልዩነቶቻችንን አጥብበን ከሕዝብ ጎን እንድንቆም ኢሕአፓ (አንድነት) ዛሬም እንደ ከዚህ ቀደሙ የተቃዋሚ ኃይሎች ኅብረት በአስቸኳይ እንዲቋቋም ጥሪውን ያቀርባል።

ሕዝባዊ ትግሉ ይቀጥላል!

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address**: **eprp-united@eprp-ihapa.com**